# <u>የወራዶችና የኦነግ ፀረ-ኢትዮጵያ</u>

# <u>ግዙፍ ውሸትና ቡፋ ፖለቲካ</u>

# <u>ሲጋለጥ</u>

*ከአስተዋይ በቀለ*

እነ ብርሃኑ፣ ኑርና ጌታቸው ለከትና ሲቪሊቲ የጐደለው የባለጌዎች ድንፋታ፣ የግዙፍ ውሸትና የቡፋ ፖለቲካ ዓይነተኛ መለዮ መሆናቸውን በቨርጂኒያ ሸራተን ሆቴል ራሳቸው እራሳቸውን አጋልጠዋል።

ለክፉም- ለደጉም ብሎ በስብሰባው ላይ የተገኘው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያየውና ያዳመጠው እነ ዶ/ር ጐብል፣ ዶ/ር ሂምለርና ወዶ አቀንቃኝ የሆነውን ዶ/ር 5ኛ ረድፍ ባንዳን ነበር።

ለሥልጣን የሚንቀራጠጠው፣ የሚቁለጨለጨውና መንገድ የሳተው አያ ብሬ ውሸት እያማጠ ሲደነፋ ላየው ምኑም-ምኑም ቁርጥ እውቁን የናዚውን ለፍላፊ ዶ/ር ጐብልን ይመስል ነበር።

አያ ኑር ደግሞ የናዚን የኤስ ኤስን ሂምለር ጨካኝ ስብእናና የዘር ትዕቢት አምላኪ መስሎ ያቺ መከረኛ የሕዝብ ውሳኔን እንደ ሽንብራ እየጠረጠረ በባሕር ዛፍ ፍሬ አልግል እንዳለ ካውያ ይለጠጥ ነበር።

አያ ጌታቸው ደግሞ እስከ ዶክተርነት ቢማርም የዘር ሙንጣዝነት አለቀው ብሎ ኢትዮጵያን ክዶ ኦነግን በማፍቀር "የኦሮሞ ሕዝብ መቶ በመቶ የኦነግ ደጋፊ ነው" ብሎ በይፋ በሐሰት እንደ መቃዲሾ ሬዲዮ ተቀደደ።

ውሻ እንኳ ስትጮህ እያየችና እያስተዋለች ነው። የጌታቸው ግን መረጃ፣ ግንዛቤና ማስተዋል የጐደለው ግዙፍ ውሸትና ቅሌት ከመሆኑ ጋር፤ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ የሥነ-ልቦና ጦርነት በይፋ ያወጀ አፋጂ አባባል ነው።

ጌታቸው ዶክተርነትን ያህል ትልቅ ትምህርት ይዞ የክሬዴንሻሉን ሙሉ ክብርና ግዴታውን መጠበቅ ሲገባው፤ ማስተዋል፣ ምላሱን መግረዝና ኢትዮጵያዊነትን ማፍቀር አቅቶት ራሱን ኦሮምኛ ተናጋሪውን ሕዝብ ያስቆጣና ያሳፈረ ግዙፍ ውሸት በገሃድ መናገሩና ቅሌት ላይ መውደቁ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አእምሮ ምንጊዜም የማይፋቅ ከፍተኛ ውርደት ነው።

*ልብ በል ኢትዮጵያዊ !*

**ደረቁ ሐቅና ተጨባጩ እውነታ ግን ጌታቸው እንደዋሸውና ኦነግ እንደሚቦተልከው አይደለም።**

ኦሮምኛ ተናጋሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ክፍል ለእናት አገሩ ኢትዮጵያ የማይገሠሥ ሕልውና፣ ብሔራዊ አንድነት፣ ለኢትዮጵያዊነትና ለአረንጓዴ- ቢጫ- ቀይ ሰንደቅ አላማ ከቀሪው ያገሪቱ የሕዝብ ክፍሎች ጋር በፅኑ የቆመ አኩሪና አስተማማኝ ኢትዮጵያዊ ነው።

ይህ ሕዝብ የገንጣይ ተባባሪ ሳይሆን፣ የአገር ወዳድና የአንድነት ኃይሎች አካል በመሆኑ እሾህን በእሾህ ብሎ ራሱ ኦነግን ነቃቅሎ ሕውልና የሚያሳጣው አጥፊው እንጂ ደጋፊው አይደለም።

በንፋስ ሽውታ አንዱ ስለሌላው ከሚሰማው በስተቀር ኦነግና ኦሮምኛ ተናጋሪው የኢትዮጵያ የሕዝብ ክፍል ግንኙነት ጨርሶ የላቸውም። ኦነግ ድጋፍና ውክልና ሊያገኝ ቀርቶ ሕዝቡንና አሠፋፈሩን እንኳ በተጨባጭ አያውቀውም።

ጌታቸው እንዳንቧረቀው ኦነግ መቶ በመቶ ድጋፍ ቢኖረው ኖሮ ሜኖሶታ ላይ መሽጐ ስትሬስ ባልበላውና ለኢሳያስ ሎሌነት አድሮ አስመራ ላይ በቦዘኔነት ባልተንከራተተና ቦምብ ረጋጭ ተብሎ በሐማሴኞች ባልተቀለደበት ነበር።

*ይህን ሐሰት ልብ በል ኢትዮጵያዊ !*

ኦነግ የሂትለርን ሰደተንላንድ ፖሊሲና የፍሬደሪክ ኒቼን የዘር ትዕቢትን በመከተል የቀዳ ስፋትና የማጆሪቲ ብዛት በሽታ በፅኑ ያደረበት ግዙፍ ውሸትንና ቡፋ ፖለቲካን ሆን ብሎ አምጦ የሚወልድና የሚያስፋፋ ተገንጣይ ነው።

ኦነግ የወራዳውን የጌታቸውን ግዙፍ ሀሰት አባባል ማጆሪቲ ነን ከሚለው ሌላ ግዙፍ የሐሰት አሀዝና ከሌለ የውሸት ቆዳ ስፋትና ክልል ጋር በማዳመር በኢትዮጵያ ሀገራዊ አፅመ-ርስትና በኢትዮጵያዊነት ላይ የታላቅነትና የአልደፈር ባይነት ግዙፍ ኢሜጅ ለመፍጠር ይሞክራል። ዓላማው የኢትዮጵያዊነትን ሥነ-ልቦና ሠብሮ ፈሪ በማድረግ የአገርና የአንድነትን ፅኑ ፍቅርና ጠንካራ ትግልን ለማስተውና ኢትዮጵያን ለማፍረስ ነው።

*ምንጊዜም አትርሳ ኢትዮጵያዊ !*

**ኦነግ በሻቢያና በዋሀቢዝም መርዝ የተበከለ፣ ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ገዥ የቆጠረ፣ ቋንቋዋን የማይናገር፣ ዜግነቷን፣ ባንዲራዋንና ፊደሏን የናቀ፣ በአንዳንድ ሕዝቦቿ ላይ አንፐሮቮክድ ጀኖሳይድ የፈጸመ ከጠላቶቿ ጋር ያበረና ሊያፈርሳት የቆረጠ መሆኑ ያለፈበት ታሪክና የራሱ ሰነዶች የሚመሰክሩት ነው።**

ደግነቱ ኦነግ የመነመነና በወያኔ ተገፍቶ የወደቀ፣ የወረቀት ነብር ሕልውና ያለው ማጠፊያውና መመለሻው የተሳናቸው ግለሰቦች በሀሡትና በሀኬት ተጠምደው የተያዙበት ሲሆን፤ ለራሱ ከመጨነቅ አልፎ ለኢትዮጵያ የሚያሰጋ አይደለም።

ከተጨባጩ የኢትዮጵያ ሁኔታና እጅግ ከላቀ የፖለቲካ ግንዛቤ ለሚነሳ የፖለቲካ ባለሟልና የሥነ- መንግሥት ኤክስፐርት ኦነግ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ስሌት ውስጥ ምንም ዓይነት ታክቲካል ወይም ስትራቴጂክ ጥቅም እንደሌለው በቀላሉ ሊረዳ ይችላል። ዋናውና ተፈላጊው ኦሮምኛ ተናጋሪው ኢትዮጵያዊ ሲሆን ይህ የሕዝብ ክፍል ደግሞ ለአገሩ ኢትዮጵያና ለአንድነቱ ፀንቶ በአስተማማኝ የቆመ ነው።

ሐቁ ይኸ ሆኖ ሳለ ኦነግን ከቁም ነገር በመቁጠር በማያሰጋው መጨነቅ፣ ግዙፍ ውሸቱን፣ ቡፍ ፖለቲካውን፣ የሀሰት አህዙንና ክሌሙን መቀበል፣ ማባበልና በሕብረት ማቀፍ የሻቢያንና የዋሀቢዝምን አፍራሽ ፖሊሲዎች በኢትዮጵያ ላይ ማራመድ ማለት ስለሚሆን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ከእያንዳንዱ አገር ወዳድና የአንድነት ኃይል ይጠበቃል።

ማንም ቢደነፋና የፈለገውን ያህል በውሸት ቢቀደድ ምንጊዜም ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያዊነትና ለሰንደቅ ዓላማ በፅኑ የቆመው ታላቁ፣ የማይበገረውና አሸናፊው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን፤ ጠንካራ ክንዱ፣ የዘለዓለም ኃይሉና ዋስትናው አገር ወዳዱና የአንድነት ኃይሉ ብቻ ነው። ድሉ ምን ጊዜም ለዚህ ኃይል ብቻ ስለሆነ ከዚህ ኃይል ጋር አሰላለፍን አስተካክሎ መቆምና መደራጀት ብሔራዊ ግዴታ ነው።

*የኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያዊነትና የሰንደቅ ዓላማ*

*ሰማዕታትን !*

*እና*

*የአርባጉጉ፣ የአሶሳ፣ የበደኖ ሰለባዎችን*

*ሁልጊዜ በሕሊና ፀሎት እናስባቸው!!*

*ምንጊዜም ኢትዮጵያ !!*

*እናሸንፋለን!!*